

ክቡር ታየ ረታ

# የኢትዮጵያን ካርታ ስራ ከመሰረቱት
# አንዱ የኢትዮጵያ ባለውለተኛ
# ታየ ረታ

## አጭር የሂዎት ታርክ ማስታወሻ

የወቅቱን ሀገራዊ ጉዳዮችን በአንጻሩ

---

**በዘውገ ፋንታ**

የቀድሞው የመሬት ይዞታ አስተዳደር
ካርታ ስራ ክፍል የበላይ (ሲንየር)
ካርቶግራፊር

### *በዚህ ጽሑፍ የተጠቀሱ ሀሳቦች*

*የክቡር አቶ ታየ ረታን ታሪክ በትቂት ገጾች ለማጠቃለል ከንቱ ሙከራ እንደሚሆን ጸሐፊው ይረዳል። በተጨማሪ፣ ከሳቸው ምግባርና ታሪክ ጋር እጅግ የተያያዙትን ጉዳዮች ጨምሮ ለማውሳት የጸሐፊው ፍላጎት ነው። ዳሩ ግን፣ ይህን አጋጣሚ በመጠቀም፣ በወቅቱ የነበሩትን ሁኔታዎች ጨምሮ ሲያቀርብ፣ አንባቢን ይጠቅማል በሚል ዕምነት ነው። ሆኖም ግን፣ በዚህ የሚቀርበው ቁንጽል ስለሚሆን፣ ይህንኑ ጸሐፊው አስቀድሞ በትህትና ይገልጻል።*

*ይህ ጽሑፉ ለአንባቢ እንዲመች በአራት ክፍል ቀርቧል። የተወሱት ታሪኮች ከክቡር ታየ ረታ የሂዎት ታሪክ ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ሁኔታ የተያያዙ ነበሩ ለማለት ሳይሆን፣ በዚያ ወቅት፣ ባንድ በኩል የተካሄደውን የወገን ጥረት፣ በሌላ በኩል ደግሞ የሆነውን ጥፋት በመጠኑ ለማንጻባረቅ ሲባል ነው።*

*ስለዚህ፣ በመጀመሪያው ክፍል፣ የኢትዮጵያን ካርታ ስራ ማን እንዳለመውና እንደጸነሰሰው፣ ከዚያም በምግባር እንዴት እንደዋለ ባጭሩ ይገልጻል። ይህ የጽሑፉ አንዱ ዋና አላማ ነው።*

*ቀጥሎም፣ ባጭሩ የኢዮጵያ የካርታ ሰፊ ስራ ጥበብና የአሰራር ስልት ባጭሩ ይገልጻል። ይኸም የጽሑፍ አላማ ነው።*

*በሶስተኛው ክፍል፣ የካርታውን ስራ መስራቾችና ገንቢዎች ከአሁኑ ደረጃ ያደረሱትን ከብዙዎቹ የኢትዮጵያ ባለውለተኞች የጥቂቶቹን ስም በመጥቀስ የሰሩትን ሰፊ ምግባር ባጭሩ ይገልጻል። የዚህ ጽሑፍ መነሻው ይኸ ነው።*

*በአራተኛው ክፍል፣ ተማሪዎች "መሬት ላራሹ" የሚለው አላማ ከከሸፈ በኋላ፣ የሀገር ጉዳይ በየቦታው እየተገረመሰ በመሄዱ፣ የኢትዮጵያ ድንበሮች ጥበቃ መገርመስስ ስላስከተለው ውዥንብር አስመልክቶ ባጭሩ ይገልጻል። በዚህ ክፍልና እላይ በተገለጹት ውስጥ፣ በወቅቱ የተገሰጹትን የኢትዮጵያ ጉዳዮች ያየውንና የሰማውን በመጠኑ ያወሳል።*

*ስለ ሀገርና ወገን እንዲሁም ስለ ቅርስ መናገርና መጻፍ፣ ሆዳሞችና ሰላቢዎች የተሰማሩበት መፈታተኛ መሆኑ ይታወቅ።*

### *ክፍል አንድ*

የኢትዮጵያን አጠቃላይ ሰፊ ምድር በተለያየ ቅርጽ በካርታ ለማሳየት አስፈላጊውን ዕቅድ የጸነሰሱትና በስራ እንዲውል ያደረጉት ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ናቸው። በዚህ ላይ የሚያሻማ ሌላ ታሪክ ያለ አይመስለም።

ጣሊያን ያልተነካ የኢትዮጵያን ሰፊ ድንግል መሬትና ማዕድን ለመጠቀም ሲል ሀገሪቱን ወደ ጎን፣ ወደላይና ወደታች እየሰነጠቀ የሚሄድ አውራ ጎዳና ለመዘርጋት፣ ከተማዎችን ለመቆርቆር፣ የዕርሻ ልማቶችን ለማስፋፋት፣ የአይሮፕላን ማረፊያወችን ለመገንባት፣ ወዘተ፣ ሲል አስቀድሞ ያዘጋጀው የሰፊ ምድሩንና አስፈላጊ የሆኑትን ጥቃቅን የመሬት ቅርጾችን የሚያሳይ ካርታ ነበር። ጣሊያን ተባሮ ሲሄድ፣ ያላቃጠላቸው ካርታና ያየር ፎቶግራፎችን ከምር ግርማይነታቸው አይተው፣ ለልማት ተቀዳሚው አስፈላጊ ምግባር ምን እንደሆነ አጥብቀው መረዳታቸውን ቀጥሎ የሆነው ሁሉ ግልጽ አድርጎታል።

ግርማዊነታቸው ከፕረዚዳንት ኬኔዲ ጋር ባላቸው ጥብቅ ወዳጅነት ምክንያት፣ ፕ/ ኬኔዲ ኢትዮጵያ እንድትለማ በጎ ነገርን ለማድረግ ፍቃዳቸውን ለንጉሥ መግለጻቸው ይታወቃል። ቀጥሎም፣ በሳቸው ፍቃድና ትዕዛዝ ዋናው ታላቅ የግንባታ ዕቅድ መሰረት የሆነው በምግባር ተፈጽሟል።

የአንድ ሀገር ማናቸውም ልማት ያለ የምድር ካርታ አይታቀድም። እንኳን ሀገር አንድ ቤትም ያለ ካርታ አይሰራም። ስለዚህ፣ የኢትዮጵያን ሰፊ ምድር አየር ፎቶግራፍ አሜሪካ አዘጋጅታ እንደምትሰጥ ለግርማዊነታቸው ቃል በገቡበት መሰረት፣ አሚሪካ የነበራትን የተክኖሎጂና የገንዘብ ኃይል፣ በዚህ ስራ እጅግ የታወቀው ያሜሪካ መንግሥት (U.S. Army, Corps of Engineers, Topographic Command Mapping Mission) የተባለው ክፍል ተመድቦ፣ የኢትዮጵያን መላ ምድር የሚያለብስ ያየር ፎቶግራፎቹን በትቂት ዓመቶች ሰርቶ አስረከበ። ኢትዮጵያ በመቶ ዓመታት የማትፈጽመው ስራ በትቂት ዓመታት ተፈጸመ። ኢትዮጵያ ያየሩን ፎቶግራፎች ወደ ካርታ ለመለወጥ የሰለጠነ የሰው ኃይል

አልነበራትም። በጣት የሚቆጠሩ በማፒንግ ሚሽኑ ሰልጥነው ስራውን ጀመሩ። ይች ቁንጽል ታሪክ የቀረበችው፣ የነዚህን ኢትዮጵያውያን ፍጹም ባለውለተኞች ታላቅ ስራ ለመግለጽ ነው። ዳሩ ግን፣ እንዲሁ በየስራው ሚና የተፈጠሩትን የስልጣኔ አራማጅ አስደናቂው ትውልድ፣ አስተማሪዎች፣ የመንግሥት ሠራተኞች፣ የአየር ሀይሉ፣ የአየር መንገዱ፣ የባህር ኃይሉ፣ የባንኩ፣ የእርሻው ልማት፣ የጎዳና ስራ፣ የከተማ ግንባታ፣ በጠቅላላ ዕድገት ከባዶ ተነስቶ እንዲስፋፋ ያደረጉትን የኢትዮጵያን ባለውለተኞች ትውልድ ጨምሮ መሆኑ ገለጻ አይሻም።

እነ አቶ ደምሰው አሳየ፣ አቶ መስፍን ወ/ማርያም፣ አቶ ታየ ረታ፣ አቶ መከብብ ማሞ፣ አቶ ኃህሉ ወልደአማኑኤል፣ አቶ አክሊሉ፣ አቶ አናጋው፣ አቶ ብርሃኑ፣ አቶ ሙሀመድ አሊ፣ ሌሎችም ከነዚህ ባላነሰ ያገለገሉት፣ የኢትዮጵያ ባለውለተኞች፣ የአየር ፎቶግራፎችን በመጠቀም የቀረውን ሰፊ የብዙ ትውልድ ምግባር ለመጀመር ኃላፊነቱን ተረከቡ። ‘አቶ’ ያልኳቸው ከጊዜ በኋላ፤ ምንስተር፣ አምባሳደር፣ ፕሮፌሰር ሌላም ከፍተኛ ባለሥልጣን መሆናቸውና እንደነበሩ ጸሐፊው ይገልጻል።

ግርማዊነታቸው የካርታው ስራ ሂደት በራሳቸው አመራር እንዲካሄድ አድርገውት ነበር። እንደ አለቃነታቸውም በየጊዜው እየመጡ ‘ምን ጎደለ?’፣ ‘ከምን ደረሳችሁ?’፣ ‘ምን ያስፈልግላችኋል?’ እያሉ የተሰራውን ስራ አይተውና ጠይቀው በርቱ! ብለው ይሄዱ ነበር።

የካርታው ድርጂት ድሮ ከነበረበት ሕንፃ ወጥቶ ከኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥቱ ጎን በተሰራው ሕንፃ እንዲገባ ንጉሡ አዘዙ። ያንን ሕንፃ ለራሱ መ/ቤት ለማድረግ ያልሞከረ ባለሥልጣን አልነበረም ተብሏል። ግን፣ ግርማዊነታቸው ‘ሌላ አፈላልግ’ እያሉ እየገለመጡ እንደመለሷቸው ተሰምቷል። ‘ካርታ ለመሞንጨር ለነሱ ይኸ ሕንፃ ኣንዴት ይሰጣል?’ እያሉ አቤቱታ ያቀርቡትንም፣ ንጉሡ በቁጣ ከስተው መለሷቸው የሚል የቡና ቤት ጨዋታም ተራብቶ ነበር። ለማጋነንም ይሁን ሳቅ ለመፍጠር፣ የካርታ ስራ የተባለውን  ያልተረዱ ሰዎች ምን እንዳሉት ወይም አሉ የተባለውን መቀለጃ እንዳረጉት ይታወሳል።

የግርማዊነታቸው የመጀመሪያ አንዱ ታላቅ ዕቅድ ተሳካ። ይኼም መላው የኢትዮጵያን ምድር ያለበሰ የተለያየ የአየር ፎቶግራፍ ተጠናቆ በመጨረሱ ነበር። በዚህ ጊዜ፣ ኢትዮጵያኖች በካርታ ስራ ትምህርት አገር ውጭ እየሰለጠኑ ተመልሰው አገራቸውን ማገልገል ጀመሩ። ቋሚ የሀገሪቱ ምድር ካርታ ስራ በዕቅድ መሰራት ተጀመረ። በተጨማሪም ልዩ ካርታዎች የመንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ሲጠይቁ ባስቸኳይ እየተሰሩ ይሰጡ ጀመር። ይህም ስለሆነ፣ ሰፊ የሀገር የተለያዩ ልማቶች በየአቅጣጫው ተጀመሩ። የግርማዊነታቸው ሁለተኛው ዕቅድ ግብ በዚህ መልክ ተፈጸመ። የመጨረሻው የግርማዊነታቸው ዕቅድ የመሬት ይዞታን አንገብጋቢ ጥያቂ ዘላቂ መልስ ለመስጠት ነበር። ለዚህም፣ የመሬት ይዞታና አስተዳደር ድርጂትን ፈጠሩ። በዚሁም መሰረት ይኸው ምኒስትሪ ከካርታና ጅኦግራፊ ክፍል ተቀላቅሎ በአዲሱ ሕንፃ ገባ። በእርሻ ምንስትርና ከሌላም ምንስቲሮች ክፍል የነበሩትን ተመሳሳይ ሙያና ስራ የነበራቸውን እየመረጡ ከመሬት ይዞታ መ/ቤት እንዲቀላቀሉ አደረጉ። የካርታ ስራው ድርጅት አንዱ ዋናው ቅርንጫፍ ሆኖ ስራው በየሚናው ቀጠለ።

የንጉሡ የረጅም ዕቅዳቸው ሊሳካና ሊፈጸም ደረሰ። ይኼም፣ ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋትን አዲስ የመሬት ይዞታና አስተዳደር ፖለሲ ለመፍጠር ነበር። ንጉሡ ይህን ደንብ አጥንቶ የሚያቀርብ አንድ የሊቃውንቶች አካል እንዲፈጠር አዘዙ። እነሱም በህግ፣ በልማት፣ በእርሻ፣ በአስተዳደር፣ እንጂነሪንግ፣ ጤና ጥበቃ በመሳሰሉት ሙያዎች የታወቁ እንዲሆኑ ግዳጅ ነበር። በዚህ ጊዜ፣ ንጉሡ ምንስትሩን አቶ ሙላቱ ደበበን በአቶ አባይ ተኩ። ለዚህም ምክንያት ነበረው። ባለሙያዎችን ክቡር ምንስትሩ መረጡ። በአንዳንዶቹ ሰዎች መመረጥ ያጉረመረሙ ባለሥልጣኖች ነበሩ። ምክንያታቸውም፣ መሬቱን ከባላባቱ እንዲነጠቅ የሚያደርጉ “መሬት ላራሹ” የሚለውን አላማ የሚያራምዱ ናቸው በሚል ፍራቻና ሀሜት ነበር። ግን በዚህ ጉዳይ ከንጉሡ ጋር በጠና እንዳይጋጩ ፈርተው አጉረምርመው ብቻ ቀሩ። የካርታ ስራዎችን አስመልክቶ ይህ ጸሐፊ ከተመረጡት አንዱ ነበር። ጥናቱ እንዲጀመርና እንዲካሄድ ትዕዛዝ ተሰጥቶ በአንድ ዓመት ውስጥ ተገባደደ። የተዘጋጀው አዲሱ የመሬት ይዞታ ህግና መመሪያ ከብዙ ዕርማት በኋላ አልቆ መጀመሪያ የምንስትሮች ካቢኔት፣ ቀጥሎም የዘውድ አማካሪዎቹ ከፈረሙበት በኋላ፣ ንጉሡ አጸደቁትና ወደ ፓርላማው ተላከ። የፓርላማ አባሎች ተወያይተውና ተሞግተው በመጨረሻ ህጋዊ እንዲሆን እነሱም ያጸድቁታል የሚል ተስፋ ነበር። ዳሩ ግን፣ በአንዱም ሀሳብ ላይ ሳይወያዩ የጽንሰ ሀሳቡ ደጋፊና ተቃዋሚ የሆኑ፣ በቡጢ ተደባደቡ ተባለ። የደከሙት ሰዎች ቀስማቸው ተሰበረ። የንጉሡ ኃይልና ሥልጣን በቀጥታ ተደፈረ፣ ተነካ። ሥልጣናቸውን የሚፈታተን አስቸጋሪ ኃይል የተፈጠረ መሰለ።

ንጉሡ በዕድሜም መግፋት ይሆናል፣ እንደ ዱሮው የሚጻረራቸውን ሰው በቁጣ “ውሰድልኝ! እንዳላየው!” ማለት አቁመው ነበር። ሲቆጡ ካባቸውን ጎንጸፍ አርገው ሽምቅቀው ጥለው መሄድ ጀመሩ። በፓርላማ ውስጥ የተካሄደውን እንደሰሙ፣ ተበሳጭተው ያለ ዕቅዳቸው ደብረ ዘይት እንደሄዱ ተወራ። የፓርላማው አባሎች  ንጉሡ ያጸደቁትን በማፍረስ ድፍረት ብቻ ሳይሆን፣ የንጉሡን ፍጹም ኃይል የሚፈታተን ስለሆነ፣ ንጉሡ ፓርላማውን እንደሚበትኑት ተገምቶ ነበር። ሳይሆን ቀረ። የንጉሡ ስልጣን ቀዳዳ እንዳለው በጠላት ታየ።

በመጨረሻም “መሬት ላራሹ” ያለፎካሪ ቀረ። ተቆርቋሪውን ‘ተራማጁ’ እንበለውና “ገበሬውን ማንቃት አለብን” የሚል ምርጫ ውስጥ ገባ። ይህ ጸሐፊ ከብዙዎቹ ተራማጅዎች ጋር ክርክር (ውይይት) በዚህ ጉዳይ ላይ እንዳደረግ ያስታውሳል።

ከነመንግሥቱ ንዋይ በኋላ፣ ንጉሡ አመጽን ወይም ረብሻን የሚቀሰቅስ ነገር እጅግ ይጠሉ ነበር። ኢትዮጵያ ሰላም ሀገር እንድትመስልና እሳቸውም በዚህ እንዲታዎቁና የክብር ሽልማት እንዲያገኙ የሚሹ መሆናቸው ይታወቅ ነበር። የአመጽ መነሻ ኣጅግ የሚረብሻቸው ጉዳይ ነበር። ለዚህ አንዱ ማስረጃ፣ ንጉሡ ባንድ ውሳኔ ላይ ያሳዩት መወላወል ነበር። ይኼም ኳስ ተጫዋቹን ነጸረን አስመልክቶ ነበር። ነጸረ በሰከረ ቁጥር ንጉሡንና ባላስልጣናትን በየመሸታ ቤቱ ይዘልፍ ነበር። አቡነ ጴጥሮስ ኃውልት አጠገብ ከነበረ ቡና ቤት በፖሊስ ተከቦ ሲዎሰድ ይህ ጸሐፊ አይቷል። በስም ማጥፋት ተወንጅሎ እንዲገረፍ ተፈረደበት። ንጉሡ አይሆንም አሉ። ዳሩ ግን፣ ተቃዋሚው በዛ። ንጉሡ ብዙ ካንገራገሩ በኋላ “***ጠንቅ ይፈጥራል ብለናል፣ አሁን እንደ አላችሁ***” አሏቸው። ነጸረ ተገረፈ። ንጉሡ የሰሜኑን ሕዝብ ያስቆጣል የሚል ፍራቻ ነበራቸው። በዚህም አልተሳሳቱም፣ ታሪክ መስክሯል።

ነጸረ ለመቀጣጫ ሲባል ጀርባውን ተገረፈ። ይህ ድርጊት እጅግ ያሳፈራቸውና የዘገነናቸው የሰሜኑ ሰዎች ውስጣዊ አመጽ ጀመሩ። ዱር ለዱር ለሚሯሯጡት ሽፍቶቹን፣ ለመርዳት መዋጮውን

በግልጽና በስውር ማጉረፍ ጀመሩ። ለሽፍቶቹ ዕርዳታ ያላደረገ የኤርትራ ተወላጅ ከተራው ሰው ጀምሮ እስከ ባለሥልጣኑ ድረስ አንድም አልነበረም ተብሏል። የኢትዮጵያ መንግሥት ሰልሎ ማስረጃ ቢሰበስብም፣ ዝም ማለት እንጂ እያንዳዱን መክበብና ማሰር ፈጽሞ የማይቻል ሆነ። የወቅቱ ፖለቲካ ያንን ድርጊት እንደማይፈቅድ፣ ንጉሡም ፈጽሞ እንደማይፈቅዱ ታወቀ። በስልጣን ላይ የነበሩት አንዳንዶቹ የተጠረጠሩት ከመንግሥት ሚስጢራዊ ስብሰባ ላይ እንዲወገዱ ተደረገ። አንዱ ከፍተኛ ባለሥልጣን የሰሜን ተወላጅ ሰው፣ ስራው ያልታወቀበት መስሎት፣ ለንጉሡ ከስብሰባ ተገለልኩ ብሎ አቤቱታ ለንጉሡ ሊያቀርብ ፈልጎ ጠየቀ። የተናደዱት ጠ/ምንስትር፣ "ንጉሡ የበላይህ አለቃ አይደሉም' ብላችሁ መልሱት" ስላሉ፣ ይኼው መልስ ተሰጠው። ደግሞ ቤተመንግሥት ሂዶ በጎን ቢጠይቅም፣ ለበላይህ አለቃ አቅርብ ተብሎ ተመለሰ። በዚህም ብዙ ስላጉረመረመ ወሬው በየቦታው ተዳርሶ ነበር። በተለይ በባለሥልጣኖቹ አካባቢ በጣም ተሰምቶ ነበር። "***ከንጉሡ ጋር አይን ለአይን እንተያይ ነበር***" ተብሎ አምሮ የተጻፈው ታሪክ ይኸ ነው!

ኢትዮጵያን ለማናጋትና ሕዝብን ለማከፋፈል የወሰዱት የቂም በቀል ርምጃ ብዙ ነበር፣ የተሳካው ግን አንዱ ብቻ ሆነ። በንጉሣዊያን ቤተሰብ ትልቅ ብጥብጥ ለመፍጠር ሴራ ተደረገ። በተለይም የተማሪዎች ንቅናቄ ከዳር እስከ ዳር ኢትዮጵያን ያናጋል ተብሎ የተጠበቀው ግን ሳይሆን ቀረ። አንድ የውጭ እጅ እንዳለበት ተጠርጥሮ ነበር። በማግስቱ ሀገር ለቆ ሄደ ተባለ።

ዋናው ቂም በቀል የተፈጸመው ግን ከብዙ ዓመታት በኋላ ነው። የነጸረ መገረፍ አሳፍሮናል የሚል ስሜት ያደረበት፣ ከዚያም ከምንስትሮች ካቢኔ ስብሰባ ልሳተፍ፣ ንጉሡንም ላነጋግር ብሎ ያልተሳካለት፣ ባደረበት ቂም ሁሉ መላው ባለሥልጣኖች እንዲጨፈጨፉ መንግሥቱ ኃ/ማርያምን አበረታቶ የኢትዮጵያን ምሶስዎችና ሀገር ጠባቂዎች ላይ ግፍ እንዲፈጸም አድርጓል ተብሏል። "**ለመሆኑ ኢትዮጵያ አሳደገችህ እንጂ ምን በደለችህ?**" ሲሉ የኢትዮጵያ አንዱ ታላቁ ምሰሶ የጠየቁት ይኸንኑ ከሀዲ ነበር። መንግሥቱ ኃ/ማርያምም እጅግ የሚጠሉትና ያወገዙት ሰው እንደሆነም ተገልጿል።

ዳሩ ግን፣ በኢትዮጵያ ሕዝብና ሀገር ጠባቂ መሪዎቿ ላይ ችግር ለመፍጠር የተነሳው የቆየ ቂምበቀል ያሰከረው ሌላ አካልም ነበር። ይኼም ኃይል፣ አጋጣሚ እየጠበቀ፣ ስልቱን በረቀቀ መንገድ እያካሄደ፣ እሳቱን እየጫረና የተጫረውን እያቀጣጠለ፣ የስራውን ጥፋት መሳካት በትቂቱ እየፈተሸ፣ አድብቶ የቆየ ሌላ ኃይል ነበር።

ኬኔዲ ከተገደሉ ጀምሮ አሜሪካ ለግርማዊነታቸው የሚያደርገው ድጋፍ በመጠኑ ቀንሶ፣ እያደረም እጅግ አነሶ ነበር። ባንዳንድ አካባቢ ግን ወዳጅነቱ በንጉሡ ብርታት ቀጥሎ መስፋፋቱ ታይቷል። ዳሩ ግን፣ በ1969 - 1970 ኢትዮጵያ የወሰደችው የውጭ ፖሊሲ አቅጣጫ፣ አሁን የምናየውና ባለፈው የደረሰባትን ከባድ ዕክል አስከትሏል። ዋናው ግልጽ መሆን ያለበት ጉዳይ፣ በጥልቅ ስልት የኢትዮጵያ ሕዝብ በማያውቀውና ጠልቆ ባልተረዳው ሁኔታ ርስ-በርሱ መተላለቁና ለዚህ ሁከት ያበቃው የኢትዮጵያ የውጭ ፖሊሲ መሆኑን ነው። በኢትዮጵያ የተከፋውን ለይቶ ማወቅ ይጠቅማል፣ ጅልና ተላላ መምሰልና በፍራቻ በመርበትበት መቀጠል፣ የሚያጠፋ የህሊና መጥፎ ድህነት ነው።

እራስንም (ሀገርን) አጥብቆ መውደድ ደግሞ ጠላት ይፈጥራል፣ በኢትዮጵያ የደረሰው ይህ ነው። ይኼንን ማወቅ ብልህት፣ ጥበብና ጽናት ነው። ሌላ የህሊና ጉድለት ካሳየን ካለንበት ሁኔታ የሚለወጥና የሚለውጠው የለም። በክቡር አክሊሉ የተመራው የንጉሡ አስተዳደር፡ ለኢትዮጵያ ጥቅም እየተባለ የተካሄደው አንዳንዱ ጉዳይ ጥላቻ ብቻ ሳይሆን ትልቅ ጠንክ ለኢትዮጵያ አትርፏል። ብዙዎቹ የኢሮፓውያን ሀገሮች ባንድ ጎራ፣ የአረብ ሀገሮች በሌላ፣ እስራኤል፣ ካናዳና አሜሪካ በሌላ መስክ ሆነው አብረው የሚሰሩበትና የማይለያዩበት አንድ የሚያደርጋቸው የጎራ የፖለቲካ ሂደት አለ። የአሜሪካ አላማ ሊመስል የሚችለው የኣስራኤል ጉዳይ ብቻ ይሆናል። በቀላሉ የሚጨበጥ ሀሳብ አይደለም፤ ምርምር ይጠይቃል። አንዱ ከተጎዳ ሌላው ጉዳቱ እኩል ይሰማዋል። አንዳቸው ቢከፋቸው ሌሎቹም አብረው ይከፋሉ ወይም አብረው ያኮርፋሉ። የልጆች ነገር ይመስላል፣ ግን ይኼን ያላወቀ እያደር ደቀቀ ማለት ነው። እስራኤል የምታደርገውን አሜሪካ ቶሎ እንዲያጸድቀው ትሻለች፣ በይፋም ትጠይቃለች። ያ-ሲሆን አሜሪካንን የሚደፍር ሳዳም ወይም ገዳፊ ይሆናል። ነገሩ፣ '*አፍንጫን ቢመቱት አይን ያነባል'*እንደሚባለው ነው።

ከዚያም ይበልጥ፣ ግብጽ የችግሯ ሁሉ መደራደሪያ ኢትዮጵያ ሆናለች። በተለይ ከወደመችበት ጦርነት በኋላ፣ ከኢትዮጵያ ያላት ጉዳይ ብቻ ነበር እንደ ሸቀጥ 'መገበያያ' አድርጋ የያዘችው። ኢስራኤል ኃይሏን ካወደመችው በኋላ፣ ኢትዮጵያን ማስፈራሪያ ኃይል አልነበራትም። ዳሩ ግን፣ "ለእኛ ይኼን፣ ለናንተ ይኼን" የሚለው የፖለቲካና የሌላ ጥቅም መገባያይዋ ኢትዮጵያ ሆና ቀጥሏል። ስለዚህ፣ ኢትዮጵያ በግብጽ ያለውን የዓለም ጻር ማመቂያ ሆናለች። ኢስራኤል የራሷ እስከተሳካ ድረስ ስለኢትዮጵያ አንድም ደንታ አይኖራትም። እስራኤሎችን የጎዳ እየመሰለው በኢትዮጵያኖች ላይ በሚድል-ኢስት የሚፈጸመው አሰቃቂ ሁኔታ መታወቅ አለበት።

እጅግ የረቀቀው የዘመኑ ስልት፣ ንጉሥ የሚያወርድ፣ ሕዝብን ከንቱ የሚያደርግ፣ ሀገርን የሚያመክን ሆኗል። በኢትዮጵያ ይህ ተፈጽሟል። ሕዝብ ራሱ ካልነቃ መሪ በቀላሉና በቅርቡ አያገኝም። ህዝብ ካልተባበረና ካልተማመነ ያለውን ያጣል። ፈጣሪ የሰጠውን ሰፊ ምድርና ጸጋ ካልጠበቀ መቀበሪያ ጉድጓድም አይኖረውም። ይኼም የሚታይ ሆኗል።

ክቡር መንግሥቱ ኃ/ማርያም፣ እጅግ አጥብቀው የሚያውቁት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ምንም የማያውቁት ጉዳይ አለ። የማያውቁት ጉድይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠልቆ የሚያውቀውን ነው። በዚህ ላይ አቶ መንግሥቱ ሊያስቡበት ይገባል።

የሰው ልጅ አንድ ጊዜ ነው የሚሞት ኢትዮጵያ ከረገመቻቸው በቀር። መለስ ዘናዊ ሁለት ጊዜ ሞቶል ተብሎ ሊታሰብ ይገባል። የቁም ህይዎቱን ከዚያም ቀሪው ስሙን ገሎ ሄዷል። ዘላቂው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንጂ ጎሳው የሚሆን ቢሆንና ከሆነ፣ የተባለው ስህተት ይሆናል። ግን መለስ የፈጠረው ስርዓት ስሙን የሚጠብቅና የሚያስተላልፍ አይሆንም፣ ዓለም ካልተበላሻና ተበላሽቶ ካልቀረ በቀር ይኸ ስርዓት ይወድማል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በአቶ መንግሥቱ ህልውና ላይ የፈረደው አለ። ሞት አይቀርምና አቶ መንግሥቱም ሲያልፉ፣ በቁማቸው እንደፈረደ በታሪካቸውም ይፈርዳል። ታሪክ የማይፍቀው ስም ትቶ መሄድ ለትውልድ አሰቃቂ ስለሚሆን አጥብቀው የሚያስቡበት ወቅት አሁን ነው። አሁን ዕድል አለ። ያንንም ኮለኔል መንግሥቱ ልባቸውና

ህሊናቸው ያውቀዋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከእርሳቸው ለመስማት የሚፈልገው ትልቅ ታሪክ አለ። ለጭካኔ ያበቃቸውን (ያዘጋጃቸውን) ለማወቅ አትብቆ ይሻል። ይኼን ለማድረግ ከምንም የበለጠ ሀገር ወዳድነት ይፈታተናል። በዕርግጥ፣ አፍ አፋቸውን የሚጠብቅ የኢትዪጵያ ጠላት (ጠላቶች) አሉ። ምናልባት የኢትዮጵያ ሕዝብ በህይወትዎ ከዚያም በኋል ለስምዎ መከታ ሊሆን ይችላል። ለዚያ ይበቃሉ የሚል ግምት የለም። ግን፣ ኢትዮጵያ እንደ መለስ ዘናዊ አይነት ሌላ አስራ ሁለት ሰይጣን መሪ ቢገጥማት፣ የርስዎን ጭካኔና በኢትዮጵያ ላይ ያመጡትን ጥፋት ፈጽሞ የሚፍቅ ወይም የሚያስረሳ እይሆንም። እንደውም ***‘’ከዚህ ጨለማ ዘመን የከተተን ማን ሆኖ?’’*** እየተባሉ በዚህ እየታወሱ ይኖራሉ። ብዙ አንብበዋል፣ ይህንና ሌላም ይረዳሉ። አሁን የሚያስፈራው፣ እርስዎ “***ስላደረግነው ታሪካ ምን ያልተናገርኩትና ያልገለጽኩት አለ*** ?” ይላሉ የሚለው ሀሳብ ነው። ይህ ይጠበቃል። ከላይ ያለውን ሀሳብ መሰንዘር ምናልባት በዕርስዎ ልቦና ፈጽሞ የማይታሰብ ድርጊት ይሆናል። እርግጥ ነው፣ በእርስዎ ቦታ መሆን ቀላል ነገር አይደለም። እርስዎ ያሉበትን ቦታና ህሊና የሚጋራ ሌላ ሰው በዚች ምድር ላይ አለ ማለት አይቻልም። ስለዚህ፣ ያሉበት ሁኔታ ሲታሰብ፣ ሊያደርጉ የሚችሉትና የማይችሉት አጠያያቂ አይሆንም። ስለዚህ የተባለው እንዳለ ሆኖ፣ የእርስዋን ጉዳይ በዚህ አጠቃሎ “የኢትዮጵያ አምላክ ይርዳዎ” በማለት ወደ ሌላው ክፍል መቀጠል ይገባል።

ክፍ ብሎ ከላይ ለተነገረው ማጠቃልያ ተደርጎ ወደ ክፍል ሶስት ይገባል። ንጉሡ በብዙ ጉዳይ ተወጥረው ነበር። ያም ሆኖ ግን ስለልማት የማይደከም ልብና ጽናት ነበራቸውና ዱሮ ያሰቡትን ዕቅድ ሊከታተሉ ተነሱ። ይኼም ከፊሉን የኢትዮጵያን የሰሜኑን ግዛት ለማልማት ነበር። ከውጭ ርዳታና ብድር ስላገኙ፣ በልማቱ ላይ በይበልጥ አተኮሩ። ጥናቱ ኤርትራ፣ ጎንደር፣ ጎጃም፣ ትግሬና ከፊል ወሎን ያጠቃልላል። እጅግ ግዙፍ ዕቅድ ከግማሽ ትሪልዮን ብር በላይ እንደሚወስድ ተገምቶ ነበር። ዕቅዱም መንገድ፣ ከተማ፣ እርሻ፣ መብራት፣ መገናኛ፣ አይሮፕላን ማረፊያ፣ ወዘተ ለማስፋፋት ነበር። ይኸ ቢሳካ ኢትዮጵያን ጥጋብ እንጂ ርሀብ የማያውቃት ሀገር እንደምትሆን ብዙ ሰዎች ተንብይተው ነበር። ከሁመራ እስከ አሰብ የሚዘረጋ ሰፊ መንገድ አንዱ ዋናው እቅድ ነበር። ዳሩ ግን፣ ጥናቱ ተጠናቆ ልማቱ በዕቅዱ መሰረት ሊጀመር ሲል፣ ኢትዮጵይያ (ንጉሡ) ሌላ ክረመት (ጠንቅ) ውስጥ ገቡ። የንጉሡ ዘመን (የኢትዮጵያ) ሁኔታ እየጨለመ እንጂ እየበራ ሳይሄድ ቀረ። የኢትዮጵያ ሕዝብ በሰንሰለት ተያይዞ የነበረው እንዳይበጠስና እንዳይበታተን ጠላቶቿም ስለማይፈልጉ፣ የቤቱ አፈራረስ በጥንቃቃ ተካሄደ። የኢትዮጵያ ታሪክ የወለደው ችግር እንጂ የውጬ ያመጣው ለውጥ እንዳይመስል ትልቅ ጥንቃቄ ነበር። በዕርግጥ የሕዝብ አብዮት ሆኖ እንዲታይ ተደርጓል፣ ሆኗልም። ምክንያቱ ሌላ ነው ቢባል፣ የሞትኩበትን በሽታ እኔ ነኝ የማውቅ፣ ማንም ቢል አልሰማም ባዩ ከታች እስከ ላይ ያለው የደርጉ፣ የሚኤሶንና የኢሐፓ ው መላው ሰማዕታቶች ይሆናሉ። ስለዚህ፣ አጥብቀን የምናውቀው፣ ሕዝብ አብዮቱን፣ አብዮቱ መንግሥቱ ኃይለማርያምን ፈጠረ ብለን ነው። መንግሥቱ ኃይለማርያም ካረዱን በስተቀር በዚህ ልቦና እንቆይ።

## ክፍል ሁለት

### *የካርታ ስራ ጥበብና ዝግጅት*

የካርታ ስራ ብዙ የተለያዩ ጥበቦችን ያካትታል። እነሱም ጂኦዶቲክ ሰርቬይ፣ ፎቶግራሜትሪ፣ ካርቶግራፊ፣ ጂኦግራፊና ሪፕሮዳክሽን የሚባሉ የስራ ጥበቦች ናቸው። በጂኦዶቲክ ሰርቬይ ክፍል የአየር ፎቶግራፎች ለካርታ ስራ የሚዘጋጁበት ሲሆን፣ ዋናው ተቀዳሚው የካርታ ስራ በዚህ ይጀመራል። በፎቶግራሜትሪ ክፍል እጅግ የረቀቁ የካርታው አቀነባበር ይካሄዳሉ። የአየር ፎቶግራፎች ተነባብረውና ተቀጣጥለው የመሬቱን ገጽ ያሳያሉ። የአየሮቹ ፎቶግራፎች ጠፍጣፋ ቢመስሉም፣ የፎቶግራሜትሪ መሳሪያዎች፣ ሜዳውን፣ ኮረብታውን፣ ሸለቆውንና ተራራውን በአይሮፕላን ላይ ተሁኖ እንደሚታይ ያደርጉታል። በመሳሪያ አማካይነት፣ የምድሩ አቀማመጥ ቅርጽ ይነደፋል።

በካርቶግራፊ ክፍል ካርታው ብዙ ነገሮችን የሚያሳይ እንዲሆን ሌላ ሰፊ ስራን ይጨምራል። ለህዝብ ጥቅም እንዲውል በተለያየ መልክና በተለያየ ቀለም ይዘጋጃል። በዚህ ላይ የሚጠቃለሉትን እጅግ ሰፊ ነገሮች በቀላሉ ለመግለጽ ባይቻልም፣ ዋናው ጥንቃቄ መጨረሻ ታትሞ የሚወጣው ካርታ አንድም ስህተት እንዳይገኝበት ማድረግ ነው። በነ ክቡር አቶ ታየ ረታና ክቡር አቶ ኃይሉ ወልደአማኑኤል የሚመራው የጂኦግራፊ ጥናት ክፍል ታላቅ ኃላፊነት ነበራቸው።

## ክፍል ሶስት

### *የኢትዮጵያ ባለውለተኞች*

ወጣት ታየ ረታ፣ በልጅነታቸው ፍየል መጠበቃቸውን ትተው በለጋ ዕድሜአቸው በአስረ-አንድ ትምህርት ጀመሩ። አዲስ አበባ መጥተው ኮተቤ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ገብተው ጨርሰው ኮሌጅ እንደጀመሩ፣ ፖይንት ፎር የተባለው የአሜሪካ የበጎ ድርጅት ስኮላርሽፕ አወጀ። በዚያ እሳቸውና ጎደኛቸው በኃላም በካርታ ድርጅት ትልቅ ኃላፊነት የነበራቸው አቶ መከብብ ማሞ ከብዙ መቶ ሰው መካከል ተወዳድረው ተመርጠው ለከፍተኛ ትምህርት አሜሪካ ተላኩ። አሜሪካ በክላርክ ዩኒቨርሲቲ ሁለቱም የባችለር ዲግሪያቸውን በጂኦግራፊ፣ በሰርቬይንግና በካርቶግራፊ አገኙ። አቶ መስፍን ወ/ማርያም ህንድ ሀገር የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ስላገኙ ወደ አሜሪካ ሂደው የማስተርስ ዲግሪ ጥናት ጀመሩ። ሶስቱም ትምህርታቸውን ጨርሰው እጅግ ወደናፈቋት ሀገራቸው ተመልሰው በካርታ ድርጅት ስራቸውን ጀመሩ። አቶ መስፍን ከትንሽ ጊዜ በኋላ በዩኒቨርሲቲው እንዲያስተምሩ ተመድበው ተዘዋወሩ። ደግሞ እንዲታወቅ ‘አቶ’ የወቅቱ የወጣቶቹ ማዕረግ ነው።

በብዙ ሀገሮች የካርታ ስራ ከመቶ ምናልባትም ባንዳንዶቹ ሀገሮች በብዙ መቶ ሰራተኞች የሚያካሂድ ነው። የኢትዮጵያ ካርታ ድርጅት ሁሉም ሰራተኛ ጸሐፊው ተላላኬው ተደማምሮ ከሃምሳ የማይበልጡ ነበሩ።

ምናልባት ኢትዮጵያኖች ባየገነዘቡትም ሌላው የውጩ ተመልካች አጥብቆ የተገነዘበው ሀቅ ኢትዮጵያኖች ያሳዩት ዕድገት፣ ቴክንዮሎጂ ያልተጨመረበት አብዛኸኛው በተፈጥሮ ችሎታ ብቻ ነበር። የቴክንዮሎጂ ጥቅም ሲያገኙ ደግሞ፣ ኢትዮጵያኖች ባጭር ጊዜ ሀገራቸው ከሌሎች በልጣና መጥቃ እንድትሄድ ያደረጓት መሆኗን ቀድሜ የጠቀስኳቸው የአየር መንገድ፣ አየር ኃይል፤ ባንክ፣ ባሕር ኃይል፣ ወዘተ ያሳዩት ዕንቁ ዕድገቶች ይመሰክራሉ። ይኸ የምንኮራበት መሆኑ ቀርቶ በተራማጆቹ ህልውና እንኳን ለማድነቅ ለማንሳትም የሚያሳፍረን ልማት ነበር። ያ-ትንሽ ኃይል (ዕንቁ ትውልድ) የቀየሰውን የ25 እና የ50 ዓመት ልማት ዕቅድ፣ ተራማጅ ነኝ የሚለው ባይተዋርና አሁን በስልጣን ያለው እያንቋሸሸ የሚናገረው ልማት ነው። ዕውነቱ ግን፣ አሁን እየተግበሰበሰ ያለው ስራ በምንና ማን ባዘጋጀው ዕቅድ ላይ መሆኑን አምነው፣ ንጉሡና የነበረው ትውልድ ካማለት ይልቅ ጣሊያን ሰራው ቢሉ ያኮራቸዋል ወይም ይቀናቸዋል። መለስ ዘናዊ፣ ሌባው መሪ፣ ዕድል ባገኘ ቁጥር ንጉሡን ከመዝለፍ ወደ ኋላ ብሎ አያውቅም።

አቶ ታየ ረታና አቶ ኃይሉ ወ/አማኑኤል በእግራቸው የረገጡትን የኢትዮጵያን ምድር ከመጥቀስ ይልቅ፣ ያልረገጡትንና ያላዩትን ምድር መጥቀስ አጭር ይሆናል። አንድ ካርታ የሚያሳየው የወንዝ፣ ሀይቅ፣ ኮረብታ፣ ተራራ፣ ሸለቆ፣ ሜዳ፣ ዱር፣ ገደል፣ መንደር፣ ታሪካው ቦታ

ስም ሁሉ፣ ትክክለኛ እንዲሆንና ባጠገቡ ያለው ኗሪ የሚጠራበት ስም መሆኑን አረጋግጠውና አመሳክረው የሚሰጡት እነሱ ነበሩ። አቶ መክብብም እንዲሁ ካርታው ዓለም አቀፍ በሚጠቀምበት ደረጃ የተጠናቀቀ መሆኑን አረጋግጠው ሲያሳልፉት ካርታው ይታተማል።

ይህ ጸሐፊ፣ ከባልደረቦቹ ጋር የቦታ ስም ጥናት ለማካሄድ በምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ሰሜንና ደቡብ ከነ አቶ ታየና አቶ ኃይሉ ጋር በመጓዝ አያሌ ጥናት በማካሄድ ለካርታው ስራ በብዙ መንገድ አበርክተዋል፣ ሀገራቸውን ዙረው ለማየትና ለማወቅ በቅተዋል።

**ክፍል አራት**

ብዙዎች ምሑራንና አገር ወዳጆች ስላገራቸው የድንበር መደፈር ምክንያት የተለያየ አስተያየት አቅርበዋል። ብዙዎች በጽሑፍም ሆነ በንግግር ያቀረቡት፣ ከሚያውቁት አንጻር በመሆኑ እጅግ ጠቃሚ ሁኗል። ዋናው ጥቅም ደግሞ፣ መላው ኢትዮጵያ ላገሩ ተቆርቋሪ መሆኑንና ለቅርሱ፣ ለታሪኩና ለትውልዱ ወደ ኋላ የማይል መሆኑን ማሳየቱ ነው። ይኽ ትልቅ አስተዋጽኦ ነው። ይህ ድርጊት የራስን መንግሥት ቅርቶ የጎረቤት መንግሥትንም በተጠንቀቅ ያቆማል። ስለዚህ፣ ይህ ጸሐፊ ያነበበውንና የሰማውን ሁሉ ያለ ነቀፌታ በአድናቆት ተቀብሎታል። ይህ የኢትዮጵያኖች ባህሪ በዚሁ መቀጠል አለበት። በዚህ ጉዳይ ላይ ስህተት የሚባል አስተሳሰብና ድርጊት የለም። ስህተት የሚባለው የመለስ ዘናዊና የሱን የከሃዲ ስራ ለማራመድ የተሰለፉት ናቸው።

አቶ መለስ እጅግ የሚዘገንን ንግግር በኢትዮጵያ መሪዎች ላይ እያሚረተ ስለ ድንበር እንደ የባዕድ ወይም የጠላት ሰው ሆኖ ተናገረ። በኢትዮጵያና ሱዳን ያለው ድንበር አይታወቅም ካለ በኋላ መሬቱን መልሰናል አለ። ይህ በስቅላት የሞት ፍርድ የሚያሰጥ ወንጀል ነው። ምናልባትም በነገሩ በመበርገግ ይሆናል፣ ብዙዎች ምሑራን ወይም ጸሐፊዎች ከመለስ ካምፕ ጭምር በሀሳቡ ተነባበሩበት። ከሽፎ የወደቀውን የግዌይንና ብዋም የተባሉት የእንግሊዝ ወታደሮች የነደፉትን እንደ አሁኑ ክልል ካርታ መሳይ እንደገና ለመመርመር ያቃጣቸው ብዙ ነበሩ። ይኽ ደግሞ ሀገርን ለመከላከል የተደረገ ሙከራ ስለሆነ አንዱም መነቀፍ የለበትም። ለነቀፌታ የሚያበቃ ስህተት አይደለም።

አሁን ያልታወቀው መታወቅ አለበት። የዚህም አጭር ጽሑፍ አላማ ይኼው ነው። በቅድሚያ በኢትዮጵያና በሱዳን መካከል የተደረጉ የድንበር ግጭቶች እጅግ ያነሱ ናቸው። እነሱም ከጦር ግጭት የሚቆጠሩ አይሆኑም። ይኽ የሚያመለክተው ኢትዮጵያና ሱዳን ሁለቱም የሚያውቁትን ድንበር ሳይጥሱ አክብረው በመኖራችው ብቻ ነው። አንዳቸውም ድንበራቸውን ባያውቁ ኑሮ ብዙ ጦርነትና ዕልቂት በየቦታው ይፈጸም ነበር። ኢትዮጵያና ሱዳን የሚያከብሩት የማይተላለፉት ድንበር ነበራቸው። አቶ መለስ ከሃዲው እንደ ባንዳ ሆኖ ይህን የድንበር ዕውቅና ሊያጠፋ ሞከረ። ኢትዮጵያና ሱዳን ድንበራቸውን በዓለም አቀፍ ዕውቅና እንዲከለል ቢሆን ኖሮ፣ መስመሩ ሁለቱም አክብረው የያዙት መስመር ይሆን ነበር። ከዚያ ውጭ ሁለቱም የኔ መሬት ብለው ማሳ የምታህል መሬት እንኳን አልተመኙም።

ኢትዮጵያም ሱዳንም በድንበር ላይ አልፎ አልፎ ጸጥታ ጠባቂ ወታደሮች ነበሯችው። ከነዚህ ጥቂቶቹን ወታደሮች ይህ ጸሐፊ በአንድ ድንበር አካባቢ አግኝቶ ሲያነጋግራቸው ከሱዳን በኩል ካሉት ወታደሮች እንደ ቅንጦት ተኩስ ወደ ሰማይ ከመተኮስ ሊላ ምንም አይነት ሽርኩቻ በመካከላቸው እንዳልነበር ገለጸዋል። እንደውም እየጠጠራሩ በቀልድ ኣንደሚያወሩ እየሳቁ አወሩ።

ይኽ ሁኔታ ደርግ ሲወድቅ እንደተለወጠ ይታወቃል። ድንበር ጠባቂዎች ግንኙነታቸው ሲቋረጥ፣ በስራቸው የሚያግዛቸው ስላጡ ጥለው እንደሄዱ ይገመታል። ከዚህ በኋላ፣ ሱዳን እየተንፏቀቀች የኢትዮጵያን መንደርና መሬት መያዟ ግልጽ ነው። በቦታው ላይ የነበሩትን ኢትዮጵያኖች እያጠፋች የራሷን መንደርና እርሻ ማስፋፋቷ ግልጽ ሆኗል። ሱዳን አጋዥ አላት። ኢትዮጵያ ግን ታዛዥና እሺ ባይ ባንዳ ነው የተቀመጠላት። አሁን እየተደረገ ያለው ሱዳን አልፋ ገብታ የያዘችውን መሬት ዕውቅ ለማድረግ ነው።

በንጉሡ ጊዜ አንዳንድ ቦታዎች በመሬቱ አቀማመጥ ምክንያት ሳያጣላቸው ቢቆዩም፣ እንዲታወቅ በ1972 ዓ/ም አካባቢ ስምምነት ተደርጓል። ይህ ጸሐፊ ካርታውን ሰርቷል። ለዚህም ተደራዳሪዎቹ ክቡር ዶ/ር ምናሴና ክብርት ዶ/ር ዮዲት ዕምሩ ነበሩ። የኢትዮጵያ ምድር ድንበር የማይታወቅ አይደለም። በኢትዮጵያ ላይ የተፈጸመው በደልና ዘረፋ የጸና ለማድረግ ጥረት አለ። ይኽም የሚቻለው ይኽንኑ ኃይል ወይም ሌላ አገልጋይ ባንዳ መሳይ በመቀያየር ይሆናል። ይኽን የሚያውቁ ዎያኔን ለመተካት ባለተስፈኞች ይኖራሉ። ምናልባት፣ የዓለም የበጎ ሕዝብ ህልውና አይሎ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነትና ዕውቅና ከጠነከረ ሁሉም ይቀለበሳል።

ደራሲው በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የቀረቡት ሀሳቦች 'የደራሲው መብት'
እንዲጠበቅ በትህትና ይጠይቃል።
ስለዚህ ጽሑፍ ጸሐፊውን ለማገኘት ከፈለጉ
zegfanta@outlook.com